August 25,2013

አጫጭር መንፈሳዊ ጽሁፎች(short devotional newsletters)

# እግዚአብሄርን መሻት

እግዚአብሄርን መሻት የበረከት ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ምድራዊ ነገሮችን መሻት በራሱ ክፉ ነገር አይደለም ግን ችግሩ የሚመጣው እነዚያ የምንፈልጋቸወ ነገሮች የሚያረኩን መስለው ከታዩን ነው፡፡በአለም ያሉ ነገሮች ጊዜያዊ ካልሆነ በስተቀር ዘለቄታዊ እርካታን አይሰጡም፡፡አደንዛዥ እጾች፣ወሲባዊ ግንኙነት ፣መጠጥ ፣አለማዊ ፊልሞች ወዘተ ለጊዜው ሊያስደስቱን ይችሉ እንደሆነ ነው እንጂ ከተወሰነ ሰአታት በኋላ ነፋስን የጨበጥን ሁሉ እስኪመስለን ድረስ ለሰማን ይችላል፡፡
በመዝ 22፡26 ላይ <<ችግረኞች ይበላሉ ይጠግባሉም እግዚአብሄርን የሚሹት ያመሰግኑታል ልባቸውም ለዘላለም ህያው ይሆናል፡፡>>የሚል አስደናቂ ቃል አለ፡፡<<ችግረኞች >> የሚለው ቃል በማቴ 5፡6 ላይ ያሉትን ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ሰዎችን ያመለክታል፡፡የተስፋ ቃሉም <<ይጠግባሉና>> የሚል ነው፡፡ይህ ተስፋ ልቤን እንዴት እንደሚያሞቀው አትጠይቁኝ፡፡
በወጤት ሂደት ባስቀምጣቸው፡ -

ችግረኞች (ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ---------->እርሱን ይሻሉ------------->ይበላሉ ይጠግባሉም--------->ልባቸው ለዘላለም ህያው ይሆናል(ድንቅ ህይወት)

ይህም ማለት አስደናቂ መንፈሳዊ ህይወት ወስጥ እንድንገባ እርሱን መሻት በህይወታችን ዋና ነገር እንደሆነ በግልጽ እናያለን፡፡<<መጥገብ>> ደግሞ ልካችን ነው፡፡በመሻት ነው ወደዚያ ልክ የምናድገው፡፡ሌላው ነጥብ መብላታችን ነው ወደ ጥጋብ የሚያደርሰን፡፡ይህ ማለት ደግሞ በእኛ በኩል ከፍ ያለ ሀላፊነት እንዳለ ይጠቁማል፡፡
መዝ 34፡10 ላይ <<ባለጠጎች ደኸዩ ተራቡም እግዚአብሄርን የሚፈልጉት ግን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጎድሉም>> የሚል ግሩም ቃል እናገኛለን፡፡በዚህ አለም በስጋ የተመቻቸው ሰዎች ብዙ ምቾት ያላቸው ቢመስልም ነፍሳቸው እጅግ ጎስቋላ መሆኗን ነው ቃሉ የሚያመለክተው፡፡በመንፈሳዊው አለም ወደ ጌታ ያልመጣ ሰው ደሀ ነው፡፡ገንዘብና ንብረት ሊኖረው ይችላል መንፈሳዊ ሰላምና ደስታ ግን በፍጹም ሊኖረው አይችልም፡፡የእግዚአብሄር ቃል ስለ እግዚአብሄር መንግስት ሲናገር ሮሜ 14፡17 ላ እንዲህ ይላል ፡-
<<የእግዚአብሄር መንግስት በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ደስታና ሰላም እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም፡፡ማለትም ባለጠጋ ሰው በስጋ ገበያ የሚገዙ ብዙ ነገሮች ቢኖሩትም በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ደስታ ግን ሊኖረው አይችልም፡፡በላይ ባለው ጥቅስ ላይ ቀጥሎ እግዚአብሄርን መፈለግ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ እንደሆነ በድፍረት ይናገራል፡፡
ሆሴ 6፡3 ላይ <<እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እንከተል እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፤እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል >> ይላል፡፡ይህ ቃል እጅግ አስደናቂ ቃል ነው፡፡መሻቱ ላለው ሰውና ለመከተል ለቆረጠ ሰው እግዚአብሄር ሊገኝ እንደሚችል በግልጽ እንዲህ ይላል፡ -
<እንደ ወገግታ ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን>>፡፡እርግጥ ነው እኛ እንወስን እንጂ በእርሱ በኩል ችግር የለም አጠገባችን ነው ያለው፡፡ስናገኘው ደግሞ ስለሚገጥመን በረከት ሲናገር <<ምድርን እንደሚያጠጣ ዝናብ ይመጣል>>ይላል፡፡ምድር በዚህ ቃል ልባችንን የሚወክል ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው ሲሆን ዝናቡ ደግሞ ልባችን ላይ ያለማቋረጥ የሚፈርፈውን የቃሉን መንፈስ ይወክላል፡፡ስለዚህ ያለመታከትና ያለማሰለስ ስንፈልገውና ስንተጋ የቃሉ መንፈስ በሚያረካን መንገድ ያጠጣንና ህይወታች ባላሰብነው መንገድ ይለወጣል፡፡እላይ ባለው ጥቅስ መሰረት <<ልባችን ለዘላለም ህያው ይሆናል>>፡፡

ስለዚህ በተግባር ደረጃ እንደዚህ እናድርግ ፡-

- በቃሉ ወስጥ እንፈልገው
- መንፈሳዊ መጽሀፍትን እየመረጥን እናንብ

- ጠንከር ያሉ የጸሎት ጊዜያትን እንያዝ

- ቢቻለን ጾምን ከጸሎት ጋር አጣምረን እንለማመድ
- ከመጽሀፍ ቅዱስ ወስጥ ጥቅሶችን እያወጣን በቂ ጊዜ ሰጥተን እናሰላስል

- ለእግዚአብሄር መንፈስ ያልተከፋፈለና የማያወላውል ልብን እንስጥ

ይህንን ብናደርግ እንደ ወገግታ እየተገኘ ያስደንቀናል!

## ጎበዝ እንገኝለት

እግዚአብሄር ሊባርከንና ሊያስደንቀን ይፈልጋል፡፡ግን ጌታ ከእኛ በቂ ጊዜን ይፈልጋል፡፡ብዙ ጽሞና፣ፊቱን ሚፈለግ፣ብዙ መቃተት እና በእግሩ ስር መሆን ያስፈልገናል፡፡መዝ 89፡20-21 ስንገኝለት ስላለ በረከት ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት ፡-

- ቅዱሱን ዘይትም ቀባሁት
- እጄም ትረዳዋለች
- ክንዴም ታጸናዋለች

ባጭሩ ሶስት በአእምሮ ለሚዳት የሚከብዱ ድንቅ በረከቶችን እናገኛለን፡-

1.የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በሀይል ወደ ህይወታችን ይመጣል

2.እርዳታውና ሞገሱ በህይወታችን በሚታይ ሁኔታ ይበዛል

3.ሚጋጋትና ጽናት የህይወታችን መለጫ ይሆናል

እነዚህ ከላይ ያሉ በረከቶች በነካ ነካ ጸሎት አይመጡም ፡፡በጸሎት የምንተጋ ሰዎች መሆን አለብን፤በጸጋው ዙፋን ፊት አብዝተን መሆን ይጠበቅብናል፡፡እንደ ጳውሎስ እና እንደ ኤጳፍራ የጸሎት ሰዎች መሆን ያስፈልገናል፡፡ያኔ ለብዙ ሰዎች የምንጠቅም የጌታ ባሪያና የክብር እቃ እንሆናለን፡፡ጌታ ሆይ ያለ መታከት ፊትህን እንድንፈልግ እርዳን!

ጌታ ሆይ ተገለጥ

እባክህ ጌታ ሆይ

ስማን እሺ በለን

እሳትህን ጣለው በመካከላችን

በረዶው ሰለቸን ከቦን በዙሪያችን

በግምባር ተደፍተው

በውነት ያማለኩህ

ክብርህን አይተው ነው

የተዋረዱልህ

ስለዚህ ተገለጥ

ተገኝተህ ገላግለን

መሮናል እሳቱ ሰዎች የለኮሱት

ቅንጣትም አልበጀን !

ማዝ 85፡ 6

<<አቤቱ ትመለሳለህ ታድነንማለህ

ህዝብህም በአንተ ደስ ይላቸዋል>>

የሚልእክቱ አዘጋጅ በቀለ በላቸው ስሆን የምኖረወም በጌትስበርግ ሜሪላንድ አካባቢ ነው፡፡በስነ-ጽሁፍና መጽሀፍ ቅዱስን በማስተማር ጌታን አገለግላለሁና ከእኔ ጋር መንፈሳዊ ስራ ለመስራት ለምታስቡና በጽሁፌ ላይ አስተያየት መስጠት ለምታስቡ በሚቀጥሉት ስልኮች እና የ ኢ-ሜይል አድራሻ ልታገኙኝ ትችላላችሁ፡፡ጌታ መንፈሳዊ ህይወታችሁን ይባርክ!